# ቀስተደመና ሬድዮ

ትችት

(17.01.03)

## ብሄራዊ ውይይት - ጊዜው ያለፈበት ወይስ ያልሰራ መፈክር???

በዜናው ላይ እንዳስደመጥነው ከአስር አመታት ጀምሮ ሲቀርብ የቆየውና በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ቅባሉት አግኝቶ የነበረው የብሄራዊ ውይይት ጥያቄ በተቃዋሚዎች ሰፈር ባልተጠበቀ ሁኔታ አወዛጋቢ ጥያቄ እየሆነ መምጣቱ ይፋ ሆንዋል ። በአንድ በኩል ሶስት ተቃዋሚ ድርጅቶች ማለትም መኢአድ፤ ኦብኮና አማራጭ ሃይሎች ይህ ጥያቄ አሁን ባለንበት የትግል ደረጃ ወደሁዋላ መሄድ ያህል ነው ሲሉ ነባሩን ጥሪ አጣጥለውታል። አልፈው ተርፈውም ይህ ጥሪ ወያኔን መለመን ያህል ነው ሲሉ ተችተውታል። ኢዴፓ በበኩሉ ደግሞ ጥሪው አሁንም ወቅታዊ ነው ካለ በሁዋላ ይህ ጥሪ እውን እንዲሆን የህዝቡ ትግል አይሎ ወያኔ እንዲቀበለው ማስገደድ ያስፈልጋል ይላል። ይህ ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ ሁለቱም ወገኖች በሌላአንድ ነገር ወይም ጥሪ ይስማማሉ። ባለፈው አስራ አምስት ቀን በሸራተን ሆቴል በኢንተር አፍሪካ ግሩፕ በተሰናዳው ስብሰባ ላይ የኢዴፓ ተወካይ አቶ መለስ ፊት ባደረጉት ንግግር ሰውየውን በሰላምና በገዛ ፈቃዳቸው ስልጣናቸውን በመልቀቅ «ታሪክ እንዲሰሩ» ጠይቀዋቸው እንደነበረ ይታወሳል። ሶስቱ ድርጅቶች ደግሞ ከዚህ አልፈው ይሄዳሉ። እነ አቶ መለስ የሚጠየቁት በገዛ ፈቃዳቸው ስልጣን እንዲለቁ ብቻ አይደለም። ላለፈውም የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ጠይቀው እንዲወርዱ ነው የተጠየቁት።

ይህ ጥሪ ጊዜ ያለፈበት ነው ወይስ ወቅታዊ? ይኸ አጉል ጸጉር የመሰንጠቅ ጥያቄ ነው። አንድ ጥሪ አስር አመት ተስተጋብቶ ፍሬ ስላልሰጠ ብቻ ጊዜው ያለፈበት ጥሪ ሊባል አይቻልም። ይህ ከተባለ ለምን ጊዜ አለፈበት? የሚለው ጥያቄና ውዝግብ ውስጥ ያስገባል ። ጊዜው አልፎበታል ወደ ሌላ መፈክር እንሸጋገር የሚል ነገር ቢመጣ እንኩዋን ችግር አለ። በዚህ አዲሱ የትግል ጥሪ እንደገና ደግሞ አስር አመት የማንኩዋትንበት ማረጋገጫ ምንድን ነው? ይህ አደጋ እንዳይደርስብን ከፈለግን አስር አመት ይዘን የተጉዋዝነውን መፈክር «ጊዜው አልፎበታል» ብለን ለመሸኘት ከመሞከር በፊት ለወደፊቱም መፈክራችን መንደርደሪያ እንዲሆነን «ያኛው መፈክራችን ለምን አልሰራም??» የሚለውን ጥያቄ መመለስ የግድ ይሆናል። ይህ ብቻ ነው ስለወደፊቱ የትግል ስልትና መፈክር ፍንጭ ሊሰጠን የሚችል ጥያቄ።

ነገሩ ጊዜ አለፈበት አላለፈበት የሚለው አወዛጋቢ ጥያቄ ነው። መፈክሩ አልሰራም የሚለው ግን አይን ያወጣ መራራ ሃቅ ነው። ከዚህ ስንነሳ ደግሞ አንድ አይቀሬ ጥያቄ መመለስ አለብን። ለምን አልሰራም?? ይህንን ጥያቄ በግልጽና በትክክል ከመለስን ሁለቱም ያስኬዳል። የብሄራዊ ውይይት ጥሪያችን እስካሁን ያልሰራባቸውን ምክንያቶች ግልጥልጥ አድርገን ካስቀመጥናቸውና ካለፉት ጉድለቶች አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመን ለመቀጠል ከቻልን አሁንም ቢሆን የብሄራዊ ውይይት ጥሪ የማይቀጥልበት ምክንያት አይታየንም። ይህንን ማስተካከል ካላደረግን ደግሞ ጥሪውን አንግቦ መቀጠል ምንም ፋይዳ የለውም። ሌላ አስር አመት እንኩዋትናለን።

ይኸ ጊዜ አልፎበታል ሌላ መፈክር እናምጣ የሚሉትም ቢሆኑ ሌላ ምርጫ የላቸውም። አዲስ በሚያፈልቁት የትግል ስልትና መስመር ለመቀጠል ያለፈው ያልተሳካበትን ምክንያት ተንትነው ማወቅና ለወደፊቱ እነዚህን ጉድለቶች አርመው ለመቀጠል መዘጋጀት አለባቸው። ከካበቱ አወንታዊም ሆኑ አሉታዊ ልምዶች ትምህርት ሳይቀስም ትግልን ማራመድ አይቻልምና ይህንን የራስ ምርምር አድርገው መራመድ ካልፈለጉ ጊዜ አልፎበታል የሚሉትን ጥሪ ትተው አዲስ አሸብራቂ መፈክር ቢያመጡም የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል አንዲት ስንዝር ወደፊት አይራመድም።

ጥያቄው እንግዲህ አልሰራም ከተባለ ለምን አልሰራም የሚለው ጥያቄ ነው። ሁለቱ
ም ወገኖች ይህ የብሄራዊ ውይይት ጥሪ ለወያኔ የሚቀርብ ማመልከቻ ሳይሆን ለህዝብ የቀ
ረበ የትግል ጥሪ ነው ብለው ያምናሉ። ይህ ልክ ነው። ሁላችንም ይህንን መፈክር እውን
ለማድረግ በህዝብ ትግል ወያኔን አስጨንቆ መያዝ ያስፈልጋል ስንል ቆይተናል። ችግሩ ህ
ዝቡ በምን ዘዴ ከዚህ ትግል ውስጥ በገፍና በአለ በሌለ ሃይሉ ይደባለቅ የሚለው ጥያቄ ነ
ው።

ደግመን ደጋግመን እንዳልነው ህዝቡ ሊንቀሳቀስ የሚችለው ተወጥሮ ከተያዘባቸው
ማህበራዊና የኢኮኖሚ የህልውና ችግሮች አንጻር አማራጭ አቅርበን እየታገልን ስናታግለው
ብቻ ነው። በዚህ መልክ ከገዛ ብሶቶቹንና ጥያቄዎቹ ተነስተን ህዝባችን በሚልዮን እየተቆ
ጠረ ከትግሉ እንዲደባለቅ እስካላደረግን ድረስ ወያኔዎችን ከስልጣን ለማባረር የሚቀረን አ
ንድ ምርጫ ለባእዳን የሚመች መፈክር እየፈለግን፤ ለባእዳንን ከወያኔ ይልቅ እኛ እንመቻ
ችሁዋለን እያልን ለነሱ አማራጭ ማቅረብ ይሆናል። ከዚህ ሌላ መፍትሄ የለም። ይቅርታ
ጠይቆም ሆነ ዝም ብሎ ወያኔ በገዛ ፈቃዱ ስልጣን ይልቀቅ በሚለው እንግዳ ጥሪ እንግፋ
ካላልን በስተቀር።

ችግሩ ህዝብን ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስ የነጻ ምርጫና የብሄራዊ ውይይት ጥሪ
ዎች እስከዚህም አይደሉም። ሌላ ጥሪ፤ ሌላ አማራጭ ያስፈልጋል። በዚህ ጉዳይ ደጋግመ
ን እንዳልነው በሃገራችን ለህዝባችን የአማራጭ ማቅረብ ችግር አለ። ከብዙ ወራት በፊት
በአንድ ዝግጅት «የአማራጭ ያለህ» በሚል ርእስ አንድ ትችት አሰደምጠናል። ይህ የአ
ማራጭ ችግር አሁንም አፍጦና አግጦ የቀረበ ችግር ነው።

ለምን አማራጭ ማቅረብ ተሳነን? ለዚህ ያሉት ሁለት መልሶች ናቸው። አንደኛ በር
እዮተ አለም ምርጫችን በወያኔ እየተተከለ ያለውን ነጻ ገበያ ተብየ አገርና ህዝብ ገዳይ ስ
ድ ስርአት ለመታገል አንፈልግም። ሁለተኛ በፖለቲካ እምነታችን ይህንን አጥፊ ኢኮኖሚ
ያዊና ማህበራዊ ስርአት የምንቃወመው ደግሞ ለስልጣን እስቅንበቃ ድረስ «አለም አቀፍ ኮ
ሙኒቲ» የምንለውን ነገር አለማስቀየም የሚል የታክቲክ ምርጫ መያዛችን ህዝባዊና አገራ
ዊ አቋዋም እንዳናንጸባርቅና ህዝባችንን እንዳንቀስቅስ አድርጎናል።

ለዚህ ለጊዜው በአንድ ምሳሌ ብቻ እንወሰናለን። ዛሬ ሃገራችን አስራ አምስት ሚል
ዮን ህዝብ ለርሃብ የተጋለጠባት አገር ነች። የኢትዮጵያ ገበሬዎች ትግላቸውን አቀነባብሮና
አማራጭ አሳይቶ የሚያታግላቸው ሃይል አለመታደላቸው ነው እንጂ ለችግራቸው መፍት
ሄው ምን እንደሆነ ያውቃሉ። ከዚህ አንጻር በቅርቡ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር
የተደረገው ጥናትና ሰፍር ቁጥር በሌላቸው የውጭም ሆነ የሃገራችን ምሁራን የተጠቆሙ
ጥናቶች ስለርሃቡም መነሻ ሆነ ስለመፍትሄውና ገበሬው ስለሚያነሳቸው አንገብጋቢ ጥያቄ
ዎች ብዙ ትምህርት የሚሰጡ ጥናቶች ይፋ አድርገዋል።

ሁሉም የመሬቱን ስሪት ለርሃቡ ተጠያቂ አድርጎ የመሬት ስሪት ይሻሻል ብሎ ጥሪ
ያቀርባል። ገበሬውም የመሬት ስሪት ይሻሻል ይላል። በዚህ በኩል የግል ሃብት የሚሉ ገበ
ሬዎች አንድ ሶስተኛ ብቻ እንደሆኑና የአብዛኛው ገበሬ ጭንቀት መሬት የመሸጥና የመለ
ወጥ መብት ይታወቅልኝ የሚል እንዳልሆነ ታይቱዋል። ጥያቄው የይዞታ ዋስትና ይረጋገጥ
ልኝ የሚል ነው። ይህ እየታወቀ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳለት የለም። ሊበራል ነኝ የሚለው
ለገበሬው መሬቱን የመሸጥና የመለወጥ መብት እታገላለሁ ይላል። ባለፈው ሰሞን በአንድ
ትችት እንዳልነው እንዲህ አይነቱ ጥያቄ ገበሬውን ያልበላው ቦታ ማከክ ነው። ችግሩ እ
ርሶ አደሩን ህዝብ በዚህ መፈክር ማንቀሳቀስ አይቻልም።

ከዚሁ ከተከሰተው ርሃብ ጋር የተያያዘ ሌላም ጥያቄ አለ። ብዙ ምሁራንና የእርሻ
ኤክስፐርቶች በወያኔ ኩባንያዎችና በድንበር ዘለል ኩባንያዎች መመሳጠር በኢትዮጵያ በገ
ፍ እየገባ ያለው የተቀየረ ዘር የሚቀጥለውን ርሃብ ያመጣል ሲሉና ሲተነብዩ ነበር። ይህ
ለርሃቡ በከፊል ተጠያቂ የሆነና ምድራችንን በማምከን ላይ ያለ ዘር በብዙ የአለም አገሮ
ች የተከለከለ ነው። በዚህ አመት እንኩዋን በደቡባዊ አፍሪካ ከባድ ርሃብ ገብቶ ሳለ በእ
ርዳታ ስም እንዳይገባ መንግስታትም ተቃዋሚ ሃይሎችም ተከላክለዋል። በኛ ሃገር ለገበሬ
ው ይህንን ጥያቄ አንስቶ የሚሙዋገት ሃይል እስካሁን አላየንም።